# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ 11-20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከጃንዋሪ 21-31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 2023
አዲስ አበባ

ማስታወሻ

እባክዎ http://www.ethiomet.gov.et ይጎብኙ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 የነበረው የአየር ....................1
ሁኔታ ግምገማ ....................1
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....................2
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....................3
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ....................4
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....................4
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ....................5
በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....................5
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....................5
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....................6
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....................6
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ....................7
ሁኔታ አዝማሚያ ....................7
ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21-02 ፌብሪዋሪ የሚኖረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ ..7
ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21-01 ፌብሪዋሪ የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....................7
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....................8


# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በጃንዋሪ ሁለተኛው አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነት ያህል በደብረብርሀን 1.0፣ 1.6፣ 2.0፣2.2፣ 2.8 እና 3.2፣ በሐሮማያ -1.4፣ -1.2፣ -0.6፣ 2.0፣ 2.4 እና 2.8፣ በቡኢ 3.0፣ 3.4፣ 3.6 እና 4.6፣ አርሲ ሮቤ 2.0፣2.5፣ 2.8፣ 3.0 እና 4.0፣ ጅማ 4.4፣ በጨፋ 2.4፣ 3.6፣3.8 እና 4.8፣ በእምድብር 4.7 እና 4.9፣ በባሌ ሮቤ 3.0፣ 3.6፣ 4.0፣ 4.6 እና 4.8፣ በእንዋሪ 4.5፣ በአደሌ 2.0፣ 2.5 እና 3.9፣ በአዴት 2.8፣ በመሐል ሜዳ 2.5፣ 4.5 እና 4.6 ፣ በአምባማርያም 4.4 እና 4.8 እንዲሁም በወገል ጤና 3.8 እና 4.4 በዲግሪ ሴልሽየስ መመዝገቡን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በጃንዋሪ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ቀናት ለዝናብ መፈጠር መንስኤ የሆኑት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከመፈጠራቸው ጋር ተያያዞ ሳሳ ያለ የደመና ሽፋን በጥቂት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በመኖሩ በጥቂት ሥፍራዎች ላይ ቀላል ዝናብ ተስተውሎባቸዋል፡፡


በአስሩ ቀናት የነበረው የዝናብ መጠን በቦታ ስርጭት አንጻር ሲገመገም ከአማራ ክልል የመካከለኛውና በሰሜን ጎንደር እና በምዕራብ ጎጃም አካባቢዎች፣ ከኦሮሚያ ክልል በቄሌም ወለጋ፣ በኢሉአባቦራ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የባስኬቶና የደቡብ ኦሞ እንዲሁም በአብዛኛው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ ከ5-28 ሚ.ሜ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1)። በዝናብ ቀናት ረገድም በአዴትና በደቡብ ኦሞ አካባቢዎች ከ2-3 ቀናት ያህል ዘንቦባቸዋል (ካርታ 2)።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር በሰሜን ጎንደር እና በምዕራብ ጎጃም፣ በቄሌም ወለጋ፣ በኢሉአባቦራ ኪስ ቦታዎች እንዲሁም በጅንካ ጣቢያ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3)።


ካርታ 1   ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር







ከመደበኛ በታች | መደበኛ | ከመደበኛ በላይ

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጃንዋሪ ሁለተኛው አስር ቀናት ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖ እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በአመዛኙ ደረቃማ የነበረው የአየረ ሁኔታ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን በተሟላ መልኩ ለማጠናቀቅ በጎ ጎን ነበረው። ይሁን እንጂ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ቀናት በጥቂት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀላል ዝናብ ተስተውሎባቸዋል፡፡ ይህም የተገኘው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት በተወሰነ መልኩ ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ሲሆን በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት አስቀድመው የበልግ ስራ እንቅስቃሴን ለሚጀምሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወን ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፈናቸው የጃንዋሪ ሁለተኛው አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖባቸው የቆየ ቢሆንም፤ በጥቂት የላይኛው ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ በጥቂት የታችኛው ኦሞ ጊቤ እና ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ሆኖም ባሳለፍናቸው አስር ቀናት የነበረው እርጥበት ከግድቦች የውሃ መጠን ቀስ በቀስ እየቀነሰ ቢሄድም፤ የጎላ ተጽዕኖ እንዳልነበረው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የተቀሩት ተፋሰሶች በአብዛኛው ቦታዎቻቸው ላይ የበጋው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ


በቀጣዮቹ አስራ አንድ ቀናት በመደበኛ ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያል::

ከዚህ ጋር ተያይዞ አሁን እየተስተዋለ ያለው የበጋው ደረቅ፣ ፀሓያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናትም ቀጣይነት እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ ይሁን እንጂ በደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከቀን ወደ ቀን እየቀነሰ እንደሚሄድ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩትና ከሚጠናከሩት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ሳሳ ያለ የደመና ሽፋን ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በጥቂት የሰሜን ምስራቅ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች ይጥቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል የሰሜን፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅና የመካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የበጋው ደርቅ፣ ጸሀያማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21-02 ፌብሪዋሪ የሚኖረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21-01 ፌብሪዋሪ የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የጃንዋሪ ወር ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛዎቹ የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን በስፋት የሚከናውኑበት ወቅት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ የበልግ ተጠቃሚ አካባቢዎች መጠነኛ እርጥበት ሊያገኙ የሚችሉበት ወቅት ነው።

ከላይ በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥሉት የጃንዋሪ ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት  በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተከናወነ የሚገኘውን የድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ ለማከናወን አዎንታዊ ሚና ስለሚኖረው አርሶ አደሮች ይህንን ምቹ ሁኔታ በአግባቡ በመጠቀም የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን እንዲያጠናቅቁ ይመከራሉ። ይሁን እንጂ በደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከቀን ወደ ቀን እየቀነሰ እንደሚሄድ የሚጠበቅ ሲሆን፤  ይህም ሁኔታ በዚህ ወቅት በመከናወን ላይ ላለው የግብርና እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። ይሁንና ከሚኖረዉ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፤ በጥቂት የሰሜን ምስራቅ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች ይጥቁማሉ፡፡ የሚጠበቀው መጠነኛ እርጥበት ለቋሚ ተክሎች እና ለተለያዩ የፍራፍሬ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን በተጨማሪም የሚጠበቀው መጠነኛ ዝናብ  የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲሻሻልና የበልግ ወቅት እርሻን አስቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወን ምቹ ዕድል እንደሚፈጥር በመረዳት አስፈሊጊውን ዝግጅት ከወዲሁ እንዲያደርጉ ይመከራል።

## ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የጃንዋሪ ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት በሰሜን ምሥራቅ፣ በመካከለኛው እና በምሥራቅና የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ እንደሚሆን ይጠበቃል። ሆኖም በጥቂት ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚኖራቸዉ ይጠበቃል፡፡ ከነዚህም መካከል በጥቂት በመካከለኛዉ አዋሽ ጊቤ፣ በላይኛው ባሮ አኮቦ፣ ዋቢሸበሌ ይገኙበታል፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች በአብዛኛው ደረቅና ከፊል ደረቅ ደረቅ ሁኔታ ያመዝንባቸዋል፡፡